ሰመጉ
HRCO

**የሰብዓዊመብቶችጉባዔ**
HUMAN RIGHTS COUNCIL

*ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው::*
**HRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.**

# ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር ሕዝብ ተስፋ የጣለበት አጋጣሚ እንዳይባክን!!

## ከሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) የተሰጠ መግለጫ

**ሰኔ 22 ቀን 2010 ዓ.ም**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብዓዊ ክብሬን ያስጠብቁልኛል ብሎ ተስፋ ያደረገባቸው በርካታ አጋጣሚዎች እንደነበሩና እነዚህ አጋጣሚዎች ግን በተለያዩ ምክኒያቶች በከንቱ መባከናቸውን ታሪክ ያስረዳል፡፡ በንጉሱ ስርዓት ገበሬው መሬት አልባ መሆኑን፣ ዜጎች የሚገባቸውን ክብር እንዳላገኙ፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የመደራጀት፣ ሀሳብን በነፃነት መግለፅ መብት መከበር እንዳለበት የተገነዘቡ የሕብረተሰብ ክፍሎች የታገሉለት ዓላማ የታሰበውን ውጤት ሳያመጣ መክኗል፡፡ ሁሉም ነገር በንጉሠ ነገሥቱ ይሁንታ የሚሰጥበት ስርዓት በሕዝብ አመፅ ሲፈርስ የመጣው የደርግ ስርዓት ሕዝብ የታገለለትን ሰብዓዊ ክብር የሚያጎናፅፍ አልነበረም፡፡ ይልቁንም መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. ባወጣው አዋጅ የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በይፋ አግዷል፡፡ የንጉሱን ስርዓት ለማስወገድ በተደረገው የህዝብ ትግል ማግስት ሲቪክ ማህበረሰቦችን ከጨዋታ ውጭ አድርጎ፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አግዶ ወደ ስልጣን የወጣው ደርግ ሕዝብ ሰብዓዊ ክብሩን ለማስጠበቅ ተስፋ አድርጎት የነበረውን አጋጣሚ አክሽፏል፡፡ የሕዝብን ተስፋ ያጨለመው የደርግ ስርዓት የፈፀማቸው ዘግናኝ ግድያዎችና ኢሰብዓዊ አያያዞችም በታሪክ ተመዝግበዋል፡፡

ከደርግ ውድቀት በኋላ በ1983 ዓም ስልጣን ላይ የወጣው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ከእነ አያሌ ጉድለቶቹ ከደርግ አንጻር ሲታይ ተስፋ የሚያጭሩ ምልክቶችን አሳይቶ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በሕግ የሳንሱር ገደብን ማንሳቱና ለሌሎች የዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እውቅና መስጠቱን እንደአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሆኖም ገና ከጅምሩም ቢሆን በርካታ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ጥሰቶች እንደነበሩ አይዘነጋም፡፡ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉም) በሕግ ደረጃ ለሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተሰጠውን እውቅና በመጠቀም፣ ነገር ግን የነበሩትን በርካታ ክፍተቶች የመሙላት አላማ አንግቦ በአገር ወዳድ ኢትዮያዊያን ተመስርቷል፡፡ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ዋና አላማውን አድርጎ የተነሳው የቀድሞው ኢሰመጉ፣ የአሁኑ ሰመጉ በፈታኝ ወቅቶች የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ሰመጉ ከተመሰረተበት ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ላለፉት 26 ዓመታት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገመንግስት ዕውቅና የተሰጣቸዉና አገሪቱ ፈርማ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና ሌሎች ስምምነቶች በኢትዮጵያ እንዲተገበሩ ያለማሰለስ ሲጠይቅ ቆይቷል፡፡ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንዲከበር፣ህጋዊና ሠላማዊ በሆነ መንገድ በነፃነት የመደራጀት መብት ዕውን እንዲሆን፣ዜጐች የፈለጉትን የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋምና ፖለቲካዊ ተሳትፎ የማድረግ መብት እንዲከበር ሰመጉ ወትውቷል፡፡ ባለፉት 26 አመታት የዜጎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር ባደረገው ከፍተኛ ትግል ዉስጥ በተለያየ ወቅት ተቋማችንን የመሩ ኃላፊዎች፣ሰራተኞች፣ አባላትና ደጋፊዎች ከፍተኛ እንግልትና ወከባ ተፈፅሞባቸዋል፣ ታስረዋል፣ ተሰደዋል፣ ዉድ የሆነውን የሕይወት ዋጋም ከፍለዋል፡፡

ተቋማችን በሀገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በትጋት እና በብቃት በመመርመር በቅድሚያ ለመንግስት ለራሱ እና ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ ቢያደርግም፤ መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ባለመስጠቱ በተለይ ባለፉት ሶስት አመታት ሁኔታዎች አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሰው ዜጎች አደባባይ በመዉጣት ከታጠቀ ሀይል ጋር ፍትለፊት

በመጋጠም ከፍተኛ ትግል አድርገዋል፡፡ በዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ዉድ ህይታቸዉን አጥተዋል፤በአስር ሺዎች ታስረዋል፤በእስር ቤት ተገርፈዋል፤ለአካላዊ እና የመንፈስ ስብራት ተዳርገዋል፡፡ ወጣቶች የችግሩ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሾች ይሁን እንጂ ያልተጎዳ የህብረተሰብ ክፍል አለ ለማለት አይቻልም፡፡

ሰመጉ እራሱም በከፍተኛ የገንዘብ እና የሰው ሃይል እጥረት ዉስጥ ሆኖ እና ሁለቱን የአስቸኳይ አዋጆች ጨምሮ ሌሎች ጫናዎች ተጨምረውበት ለዚህ ሳይንበረከክ በዚህ ፈታኝ ወቅት የመብት ጥሰቶችን ሲመረምር፤ ሲመዘግብ እና ጥሰቶቹ እንዲቆሙም ሲወተዉት ቆይቷል፡፡ ይህ የሕዝብና የተቋማት ትግል ከ27 አመታት በኂላ ሕዝብ ተስፋ የሚጥልበት ሌላ የለውጥ ጊዜን ወልደዋል::ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የገዢዉ ፓርቲ አባል ድርጅቶች አመራሮች በህዝብ ፊት በመቅረብ ላለፉት 3 አመታት ለተፈፀሙት የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ጥሰቶች ሀላፊነት መዉሰዳቸዉ እና ህዝቡን ይቅርታ መጠየቃቸዉ የለዉጡ ጊዜ መጀመሪያ ነዉ ብለን እናምናለን፡፡ የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ መንግስት የዜጎችን የዲሞክራሲ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ድክመት እንደነበረበት ከማመናቸዉም በላይ በሀገሪቱ ለዉጥ እንደሚያስፈልግና እሳቸዉም ለለዉጡ እንቅፋት ላለመሆን በማለት ስልጣናቸዉን በገዛ ፈቃዳቸዉ የለቀቁበትና በምትካቸዉ ዶ/ር አብይ አህመድ በከፍተኛ ዉስጠ-ፓርቲ ትግል አልፈዉ ወደ ስልጣን የመጡበት ሁኔታ ወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን ለማስከበር የሚያስችል አጋጣሚ መፍጠሩን የሚያሳይ መሆኑን ሰመጉ ይገነዘባል፡፡ ሕዝብ መብቱን ለማስከበርን ያሳየውን ቁርጠኝነትም ሰመጉ በእጅጉ ያደንቃል፡፡ ለከፈለው ውድ መስዋዕትነትም ትልቅ እውቅና ይሰጣል፡፡ በኢትዮጵያ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ የተደረገ መስዋዕትነት መሆኑንም ያምናል፡፡

መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን የተሾሙት ዶ/ር ዐብይ አህመድ በበዓለ-ሲመታቸው ዕለት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መስዋዕትነት ለከፈሉ ዜጎች ያላቸውን ክብር መግለፃቸውና ስለደረሰባቸዉ እንግልትም ይቅርታ መጠየቃቸው፣ በሀገራችን ዴሞክራሲን ማስፈን የሕልውና ጉዳይ መሆኑን መግለፃቸው በመልካምነቱ የሚታይ ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ በአግባቡ መተግበር እንዳለበት፣የሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተለይም ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፣የመደራጀት እና የመሰብሰብ መብቶች ሊከበሩ እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተው የገለጹበት ተስፋ ፈንጣቂ ንግግራቸው በተግባር እየተደገፈ የሚቀጥል ከሆነ ሐገራችን እና ህዝቦቿ ያሳለፉት የሰቆቃ ዘመን ወደ ማብቂያው ለመቃረቡ አመላካች እንደሆነ ሰመጉ በፅኑ ያምናል፡፡

ጠ/ሚኒስትሩ ባለፉት ጥቂት ወራት እየወሰዱት ያሉት አዎንታዊ እርምጃዎች ወቅታዊውን የፖለቲካ ትኩሳት ከማርገብ ባሻገር መንግስት የፈፀማቸውን ስህተቶችም ለማረም ጅምር እንደሆኑ ተስፋ እንድንሰንቅ አድርገዋል፡፡ በእስር ላይ የቆዩ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮችና አባላት፣ጋዜጠኞች እና አክቲቪስቶች ክሳቸውን በይቅርታ በማቋረጥ የመፍታታ ሂደቱ በስፋት እንዲቀጥል ማድረጋቸዉ፤ ለወራት የዘለቀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳ መወሰናቸዉ፤ እንዲሁም በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሀገር ያሉ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ሁሉ ወደ ሀገር ቤት ገብተዉ በሰላማዊ መንገድ እንዲታገሉ ጥሪ ማቅረባቸዉ ለሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ብሎም ለብሔራዊ እርቅ አዲስ ምዕራፍ የሚከፍቱ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ይህን አንጊ ሁኔታ ሊያደበዝዙ ወይም ሊቀለብሱ የሚችሉ ሁኔታዎች መታየታቸዉ ድርጅታችንን በእጅጉ ያሳስበዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዋናነት ከሚጠቀሱ ችግሮች ዉስጥ አሁን እየታየ ያለዉን መልካም ጅማሮ በሚፃረር መልኩ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች ኑሮአቸውን መስርተው ለአመታት ከኖሩበት ቀዬ *“የዚህ ክልል ተወላጆች አይደላችሁም”* በሚል ሰበብ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጐች ለዘመናት ከኖሩበት ቀያቸው እየተፈናቀሉ ያሉበት ሁኔታ ዋነኛዉ ነዉ፡፡ ሰመጉ የአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ጥሎበት በቆየው ገደብ እና ባለበት የበጀት እጥረት ምክንያት እስካሁን ሙሉ የመስክ ምርመራ ለማድረግ ባይችልም፤ ዜጐች ከተፈናቀሉባቸው እና በስደት ከሠፈሩባቸው አካባቢዎች ባሰባሰበው መረጃ ተፈናቃይ ዜጐች በከፍተኛ የሰብዓዊ ቀውስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያም በአለም ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ በአገር ዉስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች (IDPs) ካሉባቸዉ ሀገሮች አንዷ ሆናለች፡፡ ከእነዚህም መካከል -

- ✓ ከቤኒሻንጉል ክልል በሀይልና በግዳጅ በርካታ ዜጐች ቤት ንብረታቸውን ለቀው ተፈናቅለው በባህር ዳር ከተማ እና በተለያዩ አካባቢዎች በችግር ላይ ሲሆን ጥቃቱ እና ማፈናቀሉ አሁንም እንደቀጠለ ነው፤

- ✓ በደቡብ ክልል ጌድኦ እና ጉጂ መካከል ለረጅም አመታት ያልተፈቱ አስተዳደራዊና የተለያዩ ጥያቄዎች ምክንያት በርካታ የጌድኦ ተወላጆች ሀብት ንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል በርካቶችም ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል፤
- ✓ በጨለለቅቱ የጌድኦ ተወላጅ ያልሆኑ ዜጎችን ከከተማው እንዲወጡ ከፍተኛ ጫና እየተፈጠረባቸው ይገኛል፤
- ✓ ከቁለም ወለጋ እና ከቡኖበደሌ ዜጎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል፤

በዚህ ረገድ ክቡር ጠ/ሚንስትሩ መፈናቀሎቹ በደረሱባቸዉ አካባቢዎች በአካል በመገኘት ጭምር ድርጊቱን በጠንካራ ቋንቋ ማዉገዛቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቋም ደረጃ ግን የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት ይህንን ህገወጥ የማፈናቀል ድርጊት ለማስቆም በቂ ጥረት ሲያደርጉ አልታዩም፤ ለደረሰው ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ውድመት ኃላፊነት የሚወስድም ሆነ ሰብዓዊ እርዳታ የሚሰጥ አቅም ያለዉ የመንግስት አካል እስካሁን አልተገኘም።

በተለያዩ አካባቢዎች ከተፈፀመው ማፈናቀል በተጨማሪም

- ✓ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሲዳማ ብሔረሰብ በየአመቱ የሚያከብረውን የፍቼ ጨምበላላ በዓል ለማክበር በወጡ የሲዳማ ወጣቶች ከሰኔ 4 ቀን 2010 ዓም ጀምሮ በሐዋሳ ከተማና በሲዳማ ዞን በሚኖሩ የወላይታና ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ በተፈፀመ ጥቃት ቢያንስ የ10 ዜጎች ህይወት ጠፍቷል፤ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው በቤተ_ዕምነቶችና በትምህርት ቤቶች ተጠልለው ይገኛሉ፤
- ✓ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ከተማና በአካባቢው በብሔር የተደራጁ ወጣቶች የአማራ እና የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ በፈፀሙት ጥቃት 7 ሰዎች ተገድለዋል፤
- ✓ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማኦኮሞ ወረዳ በቶንሳ ከተማ ለጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ በተዘጋጀው የድጋፍ ሰልፍ ላይ ተካፍለው በመመለስ ላይ በነበሩ ዜጎች የክልሉ ልዩ ኃይል በከፈተው ተኩስ 2 ሰዎች ሲገደሉ ከ40 በላይ ዜጎች ቆስለዋል፤
- ✓ በኦሮሚያ ክልል ለገደንቢ እና ሻኪሶ የወርቅ ቁፋሮ የውል እድሳትና ተቃውሞ ጋር በተያያዘ በአካባቢው ነዋሪዎች ጤና እንዲሁም በቤት እንስሶቻቸው ላይ እያስከተለ ያለውን ከፍተኛ ችግር እንዲፈታ ዜጎች በሰላማዊ ሰልፍ በመጠየቃቸው በፀጥታ ሀይሎች በተፈፀመ የሀይል እርምጃ የ3 ሰላማዊ ንፁሀን ዜጎች ህይወት ማለፉ እና በበርካቶች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት እና እስራት መድረሱ ሌላዉ አሳሳቢ ሁኔታ ሆኖ ተገኝቷል።

የተጀመረዉን የለዉጥ እንቅስቃሴ ለመደገፍ እና ለማበረታታት ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በተጠራዉ በብዙ ሺህ የአዲስ አበባ እና የአካባቢዋ ነዋሪዎች የተገኙበት ትዕይንተ ህዝብ ላይ የክቡር ጠ/ሚኒስትሩ እና የስራ ባልደረቦቻቸዉ ህይወት ጭምር አደጋ ላይ ጥሎ በነበረዉ የቦንብ ጥቃት የሁለት ሰዎች ህይወት ማለፉና ከመቶ ሃምሳ ባላነሱት ላይ ደግሞ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት መድረሱ በብዙ ወጣቶች የህይወት መስዋዕትነት የመጣዉን የለዉጥ ሂደት ለመቀልበስ የሚደረግ እንቅስቃሴ እንዳይኖር በማለት ተቋማችን ይሰጋል።

በመሆኑም ለሐገራችን እና ህዝቦቿ ስር የሰደዱ ችግሮች እስካሁን ከተወሰዱት የለዉጥ እርምጃዎች የዘለለ፤ ዘላቂ እና ሁሉአቀፍ መፍትሔ እንደሚያስፈልግ ሰመጉ አበክሮ ያስገነዝባል። ለሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ ብሎም ለብሔራዊ እርቅ ያደርሳል ብሎ ሕዝብ ተስፋ ያደረገው አጋጣሚ እንዳይባክን ከመንግስት ብዙ የሚጠበቅ ቢሆንም ሌሎች አካላትም የበኩላቸዉን ገንቢ ሚና ሊጫወቱ እንደሚገባ ሰመጉ ያሳስባል። በመሆኑ

**ከመንግስት የሚጠበቅ**:

- ✓ መንግስት በተለይ በአስተሳሰባቸዉ ወይም በሚያራምዱት የፖለቲካ አቋም ምክኒያት ታስረዉ የነበሩ ዜጎችን በመፍታት እና በአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ዉጪ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ሀይሎች እንደ አገር ዉስጥ ገብተዉ በሰላማዊ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ እና ለዲሞክራሲዉ ግንባታ የበኩላቸዉን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ እያደረገ ያለዉን ጥሪ አጠናክሮ እንዲቀጥል፤
- ✓ የዜጎችን ሃሳባቸውን የመግለፅ መብት እንዲያከብር፤ ይህንኑም መብታቸውን በነፃነት የሚጠቀሙበት መድረክ ማመቻቸት እና የሃሳብ ልዩነትን ማስተናገድ የሚችል ነፃ እና ገለልተኛ ሚዲያ እንዲኖር መደገፍ፣

- ✓ የህግ አስከባሪ አካላትና ተቋማት ገለልተኛ፣ ለህግ ተገዢ እና የዜጐች መብት ጠባቂ ሆነው እንደገና እንዲደራጁ እንዲደረግ፤
- ✓ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለሚነሱ ሰብዓዊ፣ህጋዊ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችና ችግሮች ዘለቄታዊ መፍትሔ እንዲሰጥ፤
- ✓ ከህግ አግባብ ውጪ በእስር ላይ የሚገኙ ቀሪ እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤ከዚህ በኋላ የሚፈቱትም ሆነ አስቀድመዉ የተፈቱት ቢያንስ ወደ ቀድሞዉ ሕይወታቸዉ እንዲመለሱ እገዛ እንዲደረግላቸዉ፤
- ✓ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ፣የፀረ ሽብር አዋጅ፣ የፕሬስ ህጉንና ሌሎችም አፋኝ ህጎችን ቅድሚያ ሰጥቶ እንዲያሻሽል፤
- ✓ ነፃና ገለልተኛ ሚዲያዎች የሚፈጠሩበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ተፅዕኖውን ተቋቁመው በመስራት ላይ ያሉትም በነፃነት እንዲሰሩ እንዲፈቅድ፤
- ✓ በሁለቱም የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ወቅቶች የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በገለልተኛ አካል እንዲጣሩ በሩን እንዲከፍት፤
- ✓ በተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ተሳታፊ የሆኑ የመንግስት ኃላፊዎችና የአስተዳደር አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

**ከሲቪል ማህበረሰቡ የሚጠበቅ፤**

ሐገራችን ካለችበት እጅግ በርካታ፣ውስብስብ እና መጠነ ሰፊ ችግር አንፃር የሲቪክ ማህበረሰቡን ያላካተተ የመፍትሔ እርምጃ የሚጠበቀውን ውጤት ያስገኛል ብሎ ሰመጉ አያምንም፡፡ ምንም እንኳን የሲቪክ ማህበረሰቡም እራሱ ባለፉት አመታት በነበረዉ መጠነ ሰፊ እመቃ የተሽመደመደ ቢሆንም አሁን በተፈጠረዉ መልካም አጋጣሚ ሊያንሰራራ እና ከምን ጊዜዉም በበለጠ የህዝቡን የዲሞክራሲ እና የሰብዓዊ መብት ጥያቄ ከፍ አድርጎ በማሰማት ገንቢ ሚና እንዲጫወት ሰመጉ ያሳስባል፡፡

**ከተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚጠበቅ**

ክቡር ጠ/ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ከበእለ ሲመታቸዉ ቀን ጀምሮ በተለያዩ መድረኮች ለህዝብ ባደረጓቸዉ ይፋዊ ንግግሮች ሁሉ በሀገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሀገር የሚገኙ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ወደ አገር ዉስጥ በመግባት በተጀመረዉ የለዉጥ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ጥሪ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተፈጠረዉን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በአገራችን ዜጎች ሀሳባቸዉን በነፃነት የሚገልፁበት፤በአገሪቷ በሁሉም አካባቢዎች ተዘዋዉረዉ የመኖር እና የመስራት መብታቸዉ የተከበረበት ዘላቂ የዲሞክራሲ ስርዓት እንዲገነባ የበኩላቸዉን አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ሰመጉ ጥሪዉን ያቀርባል፡፡

**ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠበቅ**

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰፊ ታሪክ ያለዉ፤ የገዳ ስርዓትን የመሰሉ ጥንታዊ የዴሞክራሲ ባህል ያለዉ ኩሩ ህዝብ መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ተከታታይ ዘመናት በአገዛዞች ሲገደል፤ሲታሰር፤እና ሲሳደድ ኖሯል፡፡ በዚህም በቀላሉ የማይሽር ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ህዝቡ ዳግመኛ ወደዚህ አይነቱ የጭቆና ስርዓት ላይመለስ የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል ብሎ ሰመጉ ያምናል፡፡ በመሆኑም ህዝባችን ይህን የተፈጠረ መልካም ዕድል በብልሃት፤ በብቃት እና በሃላፊነት ስሜት እንዲጠቀምበት ድርጅታችን አበክሮ ይጠይቃል፡፡

## መልካም መፃዒ እድል ለኢትዮጵያ እና ለህዝቦቿ

ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል እና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡
: